# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::" (ኢሳ 48 ÷ 17)



God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395



ሚያዝያ 1995 April 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::" (ኢሳ 54÷13)


## እግዚአብሔርን ማወቅ

አምላካችን ከሁሉ አብልጦ ከሰው የሚሻ ው ምንድን ነው? የፈቃዱስ አሰራር እንዴ ት ነው?

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከሰው የሚ ሻው የፍቅር ወዳጅነትን ነው:: ፈቃዱም የ ተገለጠ ነው:: ነገር ግን አብዛኛው ችግራ ችን የሚከሰተው÷ ምን እንድንሠራለት እ ንደሚፈልገን ስንጠይቀው ነው:: በነጋዴነ ት÷በወንጌላዊነት÷ በሰባኪነት ወይስ በሙ ዚቀኝነት ወዘተ ጌታዬን ላገልግል? በሐገ ሬ ልቆይ ወይስ በውጭ ላገልግል? የሚሉ ትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች የብዙ ምዕመ ናን ችግር ናቸው:: ነገር ግን እግዚአ ብሔር የዕድሜ ልክ ዕቅዱን ዝርዝር ሰጥ ቶ ዞር ማለት ልማዱም÷ፍላጎቱም አይደለ ም:: በአንድ ኃላፊነት÷ወይም በአንድ ሐገ ር ለብዙ ዓመታት ሊያስቀምጠን ይችላል፡ ነገር ግን የየዕለቱን ምሪት በየዕለቱ ነው የሚሰጠን::

እግዚአብሔር የጠራን÷ጌትነቱን ጠብቀ ንና አስደስተነው÷በፍቅር ወዳጆቹ እንድን ሆን ነው:: እንደ ጌትነቱ ብንሰማውና ብን ታዘዘው ለራሳችንም ለወገንም የሚያስደን ቅ ያልታሰበ ነገር ያሰደርገናል:: እርሱን ባለማስቀደምና ባለመታዘዝ ግን በአንድ ቦታ ተወስኖ በመቅረትና ታላቅ ክብሩ በ ሕይወታችን እንዳይገለጽ ዕድላችንን ማበ ላሸት እንችላለን::

"እግዚአብሔር ለሰባኪነት ስለ ጠራኝ በሌ ላ ነገር እንዳገለግል ፈቃዱ አይደለም::"

"ያለኝ ጸጋ ___ ስለ ሆነ በተገኘው አገልግ ሎት ውስጥ መግባቴ የእግዚአብሔር ፈቃ ድ ሊሆን አይችልም" ወዘተ የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኝ ያውቃሉ ::

እግዚአብሔር ኃላፊነት ከሰጠ÷ የመፈጸ ሙንም ጸጋ ይሰጣል:: የመንፈሳዊ ስጦታ አሠራር እንዲህ ነው:: ጸጋም ከጌታ የተቀ በሉትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መለኮታዊ የዕርዳታ ኃይል ነው::

ለሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንፈልግ በዝንባሌያችን÷በችሎታችንና በ ውዴታችን ላይ ብዙ ትኩረት ማድረግ የለ ብንም:: አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ስናደርግ ደስ ስለሚለን ያ ለእኔ የእግዚአ ብሔር ፈቃድ ነው ብለን ልንሳሳት እንችላ ለን:: ይህ በራስ ወደ መታመን ሊያመራ ስለሚችል መጠንቀቅ ያሻል:: ማንም ቢ ሆን ለአገልግሎት መታመን ያለበት በጌታ ጸጋ ላይ ብቻ መሆን አለበት::

በሕይወታችን ጌትነቱን እየጠበቅን፡-"ጌ ታ ሆይ የመንግሥትህ ሥራ ከእኔ የሚፈ ልገውን ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ:: ወደምፈለግበት ሁሉ እሄዳለሁ:: በምንም ሁኔታ እከተልሃለሁ:: በእኔ የሚፈጸም ጉዳ ይ ካለህ ታዛዥ ባሪያህ ነኝ በሚል ልብ ነ ው መቅረብ ያለብን::

## ጥሪ

እግዚአብሔር ለአገልግሎት ጠርቶ ጸጋ ውን ሳይሰጥ ይቀራልን? ከአገልግሎትና ከወዳጅነቱ የቱ ይበልጣል? ለምን?

ለአሥራ ሁለት ዓመት በመጋቢነት (ቄ ስ) ባገለገልሁበት ሐገር አንድ ገበሬ ቤቱ ሂጄ እርሻውን እንድጎበኝ ጠየቀኝ:: ቤቱም እንዴት እንደምደርስ ሲነግረኝ፡- ከከተማው ወጥተህ ሩብ ማይል ያህል ንዳ÷ ከዚያም አንድ ትልቅ ቀይ የገበሬ ቤት ስታይ ወደ ግራህ ታጠፍ:: በሚቀ ጥለው መተላለፊያ መንገድ ላይ ወደ ግ ራ ታጠፍ:: በዚያ ላይ ለማይል ሩብ ጉ ዳይ ንዳ:: ከዚያም አንድ ብቻውን የቆ መ ትልቅ ዛፍ ስታይ÷ አልፈህ አራት ማይል ንዳ:: ከዚያም አንድ ትልቅ አለ ት ታገኛለህ አለኝ::እኔም በማስታወሻዬ ጻፍሁና አንድ ቀን ቀጥ ብዬ ቤቱ ደረ ስሁ::

ሁለተኛ ጊዜ ተመልሼ ስሄድ ግን ራ ሱ ገበሬው ከእኔ ጋር ነበረ::ገበሬው ወደ ቤቱ መሄጃ÷ መንገዶችን አሳምሮ ስለ ሚያውቅ÷ በተለያዩ መንገዶች ሊወስደ ኝ ይችላል:: ስለዚህ በዚህኛው ጉዞዬ ካ ርታም ማስታወሻም አላስፈለገኝም:: ባለቤቱ ራሱ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ነው:: ማድረግ የነበረብኝ አንድ ነገር ብቻ ነው:: ልብ አድርጌ በማዳመጥ በዚህ ታጠፍ ሲለኝ መታጠፍና እርሱ ያለኝን ብቻ ማድረግ ነበር::ቤቱ ያደረሰኝ ፈጽ ሞ በማላውቀው መንገድ ነበረ:: ብቻዬ ን ተመልሼ ልሄድበት እንኳ ብል የም ችል አይመስለኝም:: ገበሬው መሪዬ ነ በረ:: እርሱ መንገድ ያውቃል::

## "እኔ መንገድ ነኝ"

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተረድቶ ስለ ማገልገል አማኞች በዘልማድ የምንጠይ ቃቸው ጥያቄዎች አሉ:: ለምሳሌ ፡- "ጌታ ሆይ በምን ላገልግልህ? መቼ ል ጀምር? እንዴት? የት ቦታ? ውጤቱስ እንዴት ይሆናል? የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል::

ጌታ ዝርዝር የአገልግሎት ካርታ አስቀ ድሞ እንዲያስረክበን እንፈልጋለን:: ከ መነሣት በፊት መድረሻችንን እንጠይቃ ለን:: ጌታ ደግሞ አያስፈልግህም:: በየ ዕለቱ ተከተለኝ ይላል:: ለጌታ ክብር ማድረግ ያለብንን በእርግጥ የሚያውቅ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን? ጌታ ምን አለ? "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ" አላለምን? (ዮሐ 14÷6) መንገድን አሳያችኋለሁ÷ የመንገድ መ መሪያ ካርታ እሰጣችኋለሁ አላለም:: "እኔ መንገድ ነኝ" ነው ያለው:: ጌታ የ አገልግሎታችን ባለቤት ይሁን እንጂ እርሱ መንገዱን ያውቃል:: እርሱ ራሱ መንገዳችን ነው::

በየዕለቱ ጌታ የሚያሳየንንና የሚጠብ ቅብንን ለማድረግ ብንተጋ ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንሆና ለን:: በዚህ መልክ ጌታ እንዲመራን ል ናምነው እንችላለን? ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቀን በቀን÷ ርምጃ በእርምጃ አንተን ከ ተከተልሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስ ጥ በትክክል መሆን ስለሚቻለኝ አንተ ምራኝ፡ ልንለው እንችላለን? ይህን ማ ድረግ ከቻልን አይተን ወደማናውቀው ነፃነት መግባት ይቻለናል:: በእግዚአ ብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአ ብሔር ልጆች ይባላሉ:: ካልሆነ ግን በ ዘመናችን ሁሉ መታጠፊያ መንገድ ላ ይ በደረስን ቁጥር ግራ መጋባትና መ ጨነቅ ይሆናል:: ወሳኝ ውሳኔ ማድረግ በተፈለገበት ጊዜ ሁሉ መንቀሳቀስ ይሳ ነናል:: …

ነገር ግን እንዲህ የተምታታና የተጭ በረበረ ሕይወት እንዲኖረን የእግዚአ ብሔር ፈቃድ አይደለም::

እኔ ራሴ የሕይወቴንና የአገልግሎ ቴን መሪነት ለእግዚአብሔር ማስረከ ብ ተምሬአለሁ:: መሪነቱን ለእርሱ እ ተውና የሚያዘኝን ሁሉ በየዕለቱ በጥ ንቃቄ እፈጽማለሁ:: በየዕለቱ ለቀኑ የሚበቃ ዓላማ ያለው ኃላፊነት ይሰጠ ኛል:: እኔም በዚያን ዕለት ያለኝንና ያሳየኝን ሁሉ ፈጽሜ ከዋልሁ÷ በፈቃ ዱ ሙላት ውስጥ እንደ ዋልሁ አውቃ ለሁ:: እንዲህም ከሆነ ልዩ መገለጥና ኃላፊነት ሊሰጠኝ ቢፈልግ ዝግጁ ነኝ ማለት ነው::

## የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን ከሁሉ ይበልጣል

አምላካችን ወዳጄ ሲል የመሰከረለት አባታችን አብርሃም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው:: በኦሪት ዘፍጥረት 12 እንደምና ነበው፡- "እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባ ትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ::…" ይላል:: አብራምም ምንም ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠይ ቅ በዕምነት ወጣ:: ዘፍጥረት 12ን ስ ናነብ አብራም የተቀበለው መመሪያ በዝርዝር የተገለጸ አለመሆኑን እናያለ ን:: ከሐገርህ ውጣና ሂድ ነው የተባለ ው:: ወዴት ለሚለው ደግሞ "እኔ ወ ደማሳይህ ምድር" ነው የተባለው:: የጥሪው ዓላማ በዘመናት የሚፈጸም በረከት ነው::በዚህ ሁሉ ረዥም ዕቅድ የአብራም ድርሻ አንድ ነው:: ታዝዞ መውጣት:: የተቀረው የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው:: ዛሬ ጌታ በተመሳሳይ ሁኔታ ሲያዝዘን እናምነዋለን? የቱንስ ያህል እንታዘዛለን? ለመሆኑ መታዘዝ የዕምነት መለኪያ መሆኑን እናስተው ላለን?

ባለማመንና ባለመታዘዝ ከስንቱ በረከት ጎድለን ይሆን? አለማመናችን ስ በምን በኩል ይሆን? በተሰጠን ራዕ ይ በዕምነት ወጥቶ አለማገልገል ነው? አሥራትን በታማኝነት ወደ ቤቱ አለ ማምጣት? የበደሉንን ይቅር አለ ማለ ት? ወይም የበደልናቸውን ይቅርታ አለመጠየቅ ወዘተ ይሆንን? በምንድን ነው ቃሉን አምነን የማንታዘዘው?

አብራም ግን "በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" (ዘፍጥረት 15÷6)

"እነሆ÷ነፍሱ ኰርታለች÷ በውስጡም ቅን አይደለችም፡ ጻድቅ ግን በእምነ ቱ በሕይወት ይኖራል::"(ዕንባቆም 2÷4)

(Experiencing God በሚል ርዕስ ሔንሪ ብላካበይ እና ክላውድ ቪ ኪንግ በጋራ ከጻፉት የተአ ንጸ መጽሐፍ ተወስዶ የተዘጋጀ::)

# ብሔራዊ ንስሐና እርቅ

በዚህ ባለንበት ወር በመላው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ባሉባቸው ሌሎችም ሐገሮች ሁሉ ንስሐና እርቅ ይደረጋል፡፡

"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ÷ ፊቴንም ቢፈልጉ÷ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ ÷ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ÷ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ÷ ምድራቸውንም አፈውሳለሁ፡፡"
(መጸሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 7÷14)

በሐገራችን የሰፈነውን የርሐብና የበሽታ መዓት ማስወገድ የሚችለው አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በመረዳት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቃል መሠረት በመላው ዓለም ሕዝባችን ካያለበት ወደ እግዚአብሔር እንዲጮህ የታቀደ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁላችን የበደሉንን ይቅር እንድንልና ይቅርታም እንድንጠይቅ ይጠበቅብናል፡፡ በእነዚህ ቀናት መጾም የሚችል ሁሉ ቢጾም መልካም ነው፡፡ ይህ ዝግጅት የሚሆነው ከመጋቢት 10/1995ዓም እስከ መጋቢት 14/1995 ዓም ነው፡፡ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ተብሎ የተጻፈው የኸ ቢሆንስ ማን ያውቃል? ሁሉን ሞክረን አልሠራም፡፡ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ!! የዚህ ጉዳይ ባለ ራዕይ÷ መጋቢ ቶለሳ ጉዲና በቪዲዮ መልዕክት እንደጠየቁት÷ ኦርቶዶክስ÷ካቶሊክና÷ሁሉም ዓይነት ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያኖች በትጋት እንዲሳተፉ ተጠይቀወዋል፡፡ ይህ ዕውነተኛ የፈውስ መንገድ ነው፡፡ ሁላችንም እንሳተፍበት፡፡

(የሚከተለው ባለፈው መስከረም ወር ሰላም በሚል ርዕስ ከጻፍነው ግጥም በከፊል ነው)

መኳንንቱን ከግብፅ ብሎ ተስፋ የሰጠው ጌታ
የምድሪቱን ዕንቆቅልሽ እርሱ ራሱ እስኪፈታ
እጆቿን ወደ አምላኳ ኢትዮጵያችን ዘርግታ
ኤርትራም ከጌታ ዘንድ ምሕረትን አግኝታ
አይቀርም በእርግጥ ይመጣል ተሐድሶና ርካታ
የእግዚአብሔር መፈራት የወንጌል ብርሃን እፎይታ
የእስራኤል ቅዱስ ይባረክ ይህን የሚያደርግ ጌታ

# መንፈሳዊ ፈውስ

**የመንፈስ ቅዱስ ተግሳጽ፡-**(conviction)
መንፈሳዊ ልደት ያገኘን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በልባችን እንደሚኖር መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ በልባችን የሚኖረውም የእግዚአብሔርን ዕውነት ሊያስተምረንና ኃጢአት ስናደርግ ሊገስጽን ነው፡፡ ተግሳጹም ወደ እኛ የሚመጣው መጽሐፍ ቅዱስ ስናነብ÷ ስብከት ስንሰማ ወይም አብረውን ባሉ ወገኖች አማካይነት ሊሆን ይችላል፡፡

**ፍጥጫ፡-** (confrontation)
መንፈስ ቅዱስ ልዝብና ጨዋ በሆነው ድምጹ ሲናገረን አስተውለን ከኃጢአታችን ባንመለስ ከኃጢአታችን ጋር ያፋጥጠናል፡፡ ይህም የሚከሰተው በኑሮአችን ላይ በሚመጡ ቀውጢዎች÷ በበሽታ ወይም ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ነው፡፡

**መናዘዝ፡-** (confession)
ኃጢአት ማድረጋችንን አምነን በእውነት ከጌታ ጋር ለመስማማት መፍቀድ አለብን፡፡ "ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፡ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል፡፡" (ምሳሌ 28÷13)

**ንስሐ፡-** (repentance) ንስሐ ሰው በጥፋቱ መጸጸቱን ለአምላኩ የሚገልጽበት ሁኔታ ነው፡፡ ንስሐ ያልገባች ነፍስ ጸሎቷ ወደ እግዚአብሔር አይደርስም፡፡ ስለዚህ ይቅርታንና ፈውስን ለመቀበል ከዛሬ ጀምሬ ከኃጢአት እርቃለሁ በማለት ለእግዚአብሔር የንስሐ ቃል እንገባለን ማለት ነው፡፡

"እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርቶስን እንዲልክላችሁ÷ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም፡፡ (የሐዋሥራ 3÷19)

**ካሳ፡-** restitution
ካሳ በበደል ምክንያት የተበላሸን ወዳጅነት ለማስተካከል የሚከፈል ወይም የሚወሰድ ርምጃ ነው፡፡ ይህ በገንዘብ የሚከፈል ወይም በተግባር ሊደረግ የሚችል ነገር ከሆነ በዕውነት መደረግ አለበት፡፡ "... ወንድ ወይም ሴት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ይተላለፍ ዘንድ ሰው የሚሠራውን ኃጢአት ቢሠራ፡ በዚያም ሰው ላይ በደል ቢሆን÷ በሠራው ኃጢአት ይናዘዝ÷ የወሰደውንም በሙሉ ይመልስ፡ አምስተኛውንም ይጨምርበት÷ ለበደለውም ሰው ይሰጠው፡፡ ነገር ግን ይመልስለት ዘንድ ሰውየው ዘመድ ባይኖረው÷ስለ በደል ለእግዚአብሔር ይመልሰው..." (ዘኁልቍ 5÷5-8)

**ይቅርታ (ምሕረት)፡-**
በዕውነት ከልብ ተናዝዘን ንስሐ ከገባን፡ በመስቀል ላይ ከፈሰሰው የኢየሱስ ደም የተነሣ ሙሉ ይቅርታ እንደተሰጠን ማመን እንችላለን፡፡ ምሕረትን በዕምነት ተቀብለን ከኩነኔ ነፃ መውጣት አለብን፡ የበደልነው ሰውን ከሆነ እንደ እግዚአብሔር በአንዴ ላይረሳልን ይችላል፡፡ ራሳችንም ላንረሳ እንችላለን፡፡ ሆኖም ፍቅርንና ወዳጅነትን እንደ አዲስ በይቅርታ መጀመር ያስፈልጋል፡ይቻልማል፡፡

**መታረም፡-** discipline
ከኃጢአት ወይም ከጉልህ በደል ስንመለስ የሥነ ሥርዓት (የመታረም) ርምጃ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ርግጥ የኃጢአታችን ሁሉ ዋጋ በቀራኒዮ መስቀል ተከፍሎአል፡፡ ይሁን እንጂ ኃጢአት በሰዎች መሐከል የሚፈጥረውን ቀውስ በሚታይ አኳኋን ለመፍታት÷ በደለኛው ወደ ቀደመው ሥፍራው ሳይመለስ ሃሳቡን ወደ መልካም መለወጡን የሚያሳይ÷የመታረም ጊዜ መወሰድ አለበት፡፡

**እርቅና መልሶ መቋቋም፦**
reconciliation/ restoration

በዚህ ደረጃ ላይ የእግዚአብሔርን ኃይልና ተዓምራት በሕይወታችን÷በትዳራችን÷በኅብረታችን ወይም በማንኛውም ነገራችን መጠባበቅ እንችላለን፡፡ ሐቀኛ ስምምነትንና አንድነትን በመቻቻል እየጠበቅን አስደናቂውን የእግዚአብሔር እጅ መገለጥ መጠበቅ ነው፡፡ ጌታም አይዘገይም፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

# ፋሲካችን ክርስቶስ

"እግዚአብሔር በግብጽ ሐገር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡-... በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት...ይውሰድ፡፡... እያንዳንዱም እንደሚበላው መጠን ከጠቦቱ ይካፈሉ፡፡ የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት... ይሁን፤... የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት፡፡ ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቅቡት፡፡ ... እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው፡፡እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ ሐገር አልፋለሁ÷ በግብፅም ሐገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኩርን ሁሉ እገድላለሁ፤ በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ደሙን ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ፤እኔም የግብፅን ሐገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም፡፡" (ኦሪት ዘጸአት 12÷ 1 - 13)

ውድ ወገኖቼ፡- በዓለም ላይ የሚመጣው ፍርድ በግብፅ ላይ ከሆነው ፍርድ ይከፋል፡፡ የማይዋሸውና ፡ የማይሻረው የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ስሙ፡- "እነሆ፥ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል፤ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች÷..." (ትንቢተ ሚልክያስ 4÷ 1 - 2)

የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ÷የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመቃንህና በጉበንህ አለ? ሕዝበ እስራኤል ያደርግ እንደነበረው÷በየዓመቱ የበግ ኰርማ ማረድ አያሻም፡፡ አይጠቅምም፡፡ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና" (1ቆሮ 5÷7)

የኢየሱስ ወዳጅ ነህ? ጥያቄዬ ኃይማኖትህ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ አይደለም፡፡ ኃይማኖተኛነት አያድንም፡፡ ጌታ ኢየሱስንም የሰቀሉት ኃይማኖተኞች ነበሩ፡፡ ነገር ግን የሞት መልዓክ ዛሬ ቢመጣ ወደ ቤትህ እንዳይገባ የሚከላከል አለህ? አስተውል፡፡ የፍርድ ቀን ሩቅ አይደለም፡፡ የማይታዘዙት ይፈረድባቸዋል፡፡




የተሰቀለውን÷ እግዚአብሔርም ከሞት ያስነሣውን ኢየሱስን "ለተቀበሉት ሁሉ ግን÷በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" (የዮሐንስ ወንጌል 1÷12)

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡"(የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

**የንስሐ ፀሎት፡-** እግዚአብሔር ሆይ÷ሰለ ኃጢአታችን ተፈርዶበት በቀራንዮ መስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ለእኔ እንደ ሞተ አምናለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብና ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ በመገኘት ፡- የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅና ለመከተል እተጋለሁ፡፡ ያለፈውን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡፡ በመንግሥትህም ተቀበለኝ፡፡ ስለ ስምህ፡፡ አሜን፡፡
ኢየሱስ ጌታ ነው፤ ጌታ ይባርክህ፡፡